# እነሆ ቅኔ፣ ዝም አልል እኔ

በኮስሞስ-2000(ኦገስት 2010)

የምወደው ጓደኛ፣
ሲጠይቀኝ በትግርኛ፣
መልስ ሰጠሁት በአማርኛ።
"ጣና ከመይ እሎ?" ቢለኝ፣
ግብፆችን ጠይቅ አልኩኝ።

የደጋው መንገድ ሜዳማ፣
የቆላው መንገድ ገደላማ።
ወያኖች ሄዱ ደጋ ደጋውን፣
ቀን ዐይተው ገደሉን።

እርስታችሁን አካፍላችሁ፣
ልጆቻችሁን ድራችሁ፣
በላይ ሆነው በደሏችሁ::
ዳግም ሲመጡ ካያችሁ፣
አስተናግዷቸው ደግናችሁ::

ወያኖች ሰክረው ከተጣሉ፣
እናስታርቅ አትበሉ።
መሸታ ቤት ገብተው፣
ዕርቅ ይወርዳል ሲያጠጣው።

አቁም አልኩህ ቀልዱን፣
የሚስቅ ሰው የለም።
የሚያዳምጡህ ገብተው፣
ወያኔዎች ብቻ ናቸው።
ደግሜ ልንገርህ አንተ ሰው፣
ይስቁብናል በልተው።

የድሮ ሰዎች ሲነግዱ፣
በበቅሎ ነበር የሚሄዱ።
የዛሬው ዘመን ይፈጥናል፣
አየር ባየር ሆኗል።

የጓሮዬን ፍራፍሬ፣
እየሠረቁት ተቸግሬ፣

ጠባቂ ቀጠርሁ ዘበኛ፣
ሌሊት ደክሞት ሲተኛ፣
እየሰለለ የገባው፣
ብስል፣ ብስሉን ለቀመው።

ሦስት ወረዳዎች የወሰዱ፣
እራሳቸውን ቢወዱ።
ከለም መሬቱ ሲደርሰው፣
ሱዳንም ደስ አለው።
ጎንደሮች አጡ አሉ መኖሪያ፣
ጉልበት ጠፍቶ ማስከበሪያ።
አርበኞች ገቡ ከዱሩ፣
የብረት አጥር ሊሠሩ።

መለስ ሆይ!
ሊሄዱ ነው ወይ ትተውን?
ልናነጋግርዎ እየጠበቅን።
ይበሉ ይሂዱ ከቸኮሉ፣
በምንጠራዎ ጊዜ ይመጣሉ።

ከአባ ጳውሎስ ሃውልት ሥር፣
ይጣላል አሉ ብር።
ጣያት አምላኪዎች በሙሉ፣
ድፍን መቶ ብር ይጥላሉ።
መቶ መቶውን ሰብስበው፣
ያመነዝራሉ አሉ መነኩሴው።